# የኢትዮጵያ የከተሞች ቀን
# ETHIOPIAN CITIES' DAY ፬

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብ
የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር

Ethiopian Cities' Network

gtz

# ሁለተኛዉ የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን

## “ፈጣን የከተሞች ዕድገት ለፈጣን ሀገራዊ ልማት”

### ዋና አዘጋጆች

የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር
የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ
የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር

### ተባባሪ አዘጋጅ

ጂቲዜድ ያልተማከለ የከተማ አስተዳደር ፕሮግራም

ከህዳር 16 — 20 ቀን 2003 ዓ.ም
ሐዋሳ

# ሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ ፈጣን የከተማ ህዝብ እድገት ከሚያስመዘግቡት የአለም ሀገሮች አንዷ ናት፡፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በኢትዮጵያ በከተሞች የሚኖረው ህዝብ በዓመት በአማካይ በ4%[1] ያድጋል፡፡ ይህ ፈጣን እድገት በከተማ የሚወለዱ ህፃናትና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ የህዝብ ፍልሰት ድምር ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በከተማ የሚኖረው ህዝብ ብዛት 12 ሚሊዮን[2] አካባቢ የሚገመት ሲሆን የህዝብ ቁጥር እድገቱ በዚህ ከቀጠለ እ.ኤ.አ. 2015 በኢትዮጵያ ከተሞች የሚኖረው ህዝብ ወደ 17.8 ሚሊዮን[3] እንደሚጠጋ ይገመታል፡፡

ይህ ፈጣን የከተማ ህዝብ እድገት በኢትዮጵያ ከተሞች እንዲስፋፉ የሚያበረታታ በጎ ገፅታ አለው፡፡ የከተሞች መስፋፋት ለኢንዱስትሪና አገልግሎት ክፍለ ኢኮኖሚው እድገት ወሳኝ ነው፡፡ በተጨማሪም ከተሞች በገበያ ማዕከልነታቸው ለእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚ መጠናከር የላቀ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡ ከተሞች የባህል፣ የምርምር እና የስልጣኔ ማዕከልም ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት የከተማ ነዋሪው ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 16%[4] ብቻ ቢሆንም ከተሞች ለዓመታዊ ኢኮኖሚ ምጣኔው የሚያበረክቱት ግብአት 66%[5]ያህል እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይህም ከተሞች ለኢኮኖሚው እድገት ያላቸው የጎላ አስተዋፅኦ የሚያመላክት ነው፡፡

የከተሞች መስፋፋት ይህን መሰል በርካታ ጠቃሚ ጎኖች ቢኖሩትም በአንፃሩ ከተሞቻችን ለረጅም ጊዜ ተገቢውን ትኩረት ሳያገኙ በመቆየታቸው በፍጥነት በማደግ ላይ ለሚገኘው የከተማ ነዋሪ ህዝብ በቂና ደረጃውን የጠበቀ የመሰረተ ልማትና የማህበራዊ አገልግሎት ለመስጠት አዳጋች ሆኖባቸው ቆይቷል፡፡ ይህንን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብና ከተሞች ለአጠቃላይ የሀገሪቱ እድገት ያላቸውን ወሳኝ ሚና በመረዳት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የከተማ ልማት ፖሊሲ እንዲሁም የከተማ መልካም አስተዳደርና የልማት ኘሮግራሞችን ነድፎ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ የከተማ ልማት ፖሊሲዉና የተዘጋጁት የልማት ኘሮግራሞች አፈጻጸማቸው እንዲያድግ የህብረተሰቡም በከተማ ልማት ላይ ያለው ግንዛቤ እንዲሰፋ እና ተሳታፊነቱም እንዲጎለብት ህዳር 17 ዓመታዊና ብሔራዊ የከተሞች ቀን በአል ሆኖ እንዲከበር ተሰይሟል፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ የመጀመሪያ ከተሞች ቀን በ2002 ዓ.ም. በሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር አዘጋጅነት በአዲስ አበባ ከተማ መከበሩ ይታወሳል፡፡ የሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በዓል በፌደራል የሥራና ከተማልማት ሚነስቴር ፣በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መደረክ እና በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር አዘጋጅነት በሀዋሳ ከተማ ከህዳር16 - 20 የሚከበር ይሆናል፡፡

## 2. ዓላማ

### 2.1 ጥቅል ዓላማ

የከተማ ነዋሪዎችን፣መንግስትና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማጠናከር፣መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት እንዲሁም እሴቶቻቸውን በማስተዋወቅና በማጎልበት የከተማ ልማት ፖሊሲውን እና ሌሎች የከተማ ልማት ኘሮግራሞችን ትግበራና ስኬት ማፋጠን፡፡

### 2.2 ዝርዝር ዓላማዎች

1. የከተማ ልማት ፕሮግራሞችን ለከተማ ነዋሪዎችና ለባለድርሻ አካላት በማስተዋወቅ ቅርርብ መፍጠርና ማጠናከር ፣
2. በከተሞች መሀከል ትውውቅ፣ትብብር እና ጤናማ ውድድር በመፍጠርና በማጎልበት የከተሞች የልማት ስኬት ማፋጠን፣
3. ከተሞቻችን በልማት ሂደታቸው ያስመዘገቧቸውን መልካም ተሞክሮዎችና ልምዶች በአግባቡ መቀመርና ማስፋፋት፣
4. የኢትዮጵያ ከተሞችን በጎ ገፅታ በማስተዋወቅ ከተሞች ከኢንቨስትመንትና ቱሪዝም ዘርፎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፡፡

---
[1] ዘልድቅፕ፡ የከተማ ልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ኘሮግራም
[2] 2007 - የህዝብና ቤት ቆጠራ 1999ዓ.ም.
3 ዘልድቅፕ- የከተማ ልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ኘሮግራም
4 2007 - የህዝብና ቤት ቆጠራ 1999ዓ.ም.
5 ዘልድቅ - የከተማ ልማትና የመልካም አስተዳደር ኘሮግራም

## 3. የሚጠበቁ ውጤቶች

1. የኢትዮጵያ ከተሞች ሥራዎቻቸውን በተለያየ መድረክ ያቀርባሉ፣ ልምዶችን እና መልካም ተሞክሮዎችንም ይለዋወጣሉ፣
2. ከተሞች በጎ ገጽታቸውን ያስተዋውቃሉ በዚህም የኢንቨስትመንት፣የገበያና የቱሪዝም ተጠቃሚ ይሆናሉ፣
3. በከተሞች መካከል ጤናማ የእድገት ፉክክር ይፈጠራል፣ ይስፋፋል፣
4. የከተማ ነዋሪዎች ስለከተሞቻቸው ስራዎች መረጃ የሚያገኙበትና ግንዛቤ የሚያሰፋበት መድረክ ከመሆኑም በተጨማሪ የባለቤትነትና የተሳታፊነት ስሜት ይፈጠራል፣
5. በከተሞች መካከል የተፈጠረው ትስስር ይበልጥ የተጠናከረና ስፋት ያለው ይሆናል፣
6. ስራ ፈጣሪነት ብሎም ለከተማ ልማት ግብአት የሚሆኑ አዳዲስ ፈጠራዎች እና ሀሳቦች የሚበረታቱበት እና የሚዳብሩበት መድረክ ይፈጠራል፡፡

## 4. የሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን መሪ ቃል

ሁለተኛዉ የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን *“ፈጣን የከተሞች ዕድገት ለፈጣን ሀገራዊ ልማት”* በሚል መሪ ቃል በሀገርአቀፍ ደረጃ ይከበራል፡፡

## 5. የሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን የክብረ በዓል ወቅት

ሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በዓል ከዋዜማው ህዳር 16 እስከ ህዳር 20 ቀን 2003 ዓ.ም. በሀዋሳ ከተማ ይከበራል፡፡

## 6. የሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በዓል ተሳታፊዎች

- 82 የሚደርሱ የኢትዮጵያ ከተሞች (በሀገር አቀፍ ደረጃ በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን የተሳተፉ 43 ከተሞች እና 39 አዳዲስ ከተሞች)፣
- የከተማ ነዋሪዎች፣
- የልማት አጋሮች/ሲቪክ ማህበራት፣ መንግስታዊ ተቋማት፣ የትምህርት ተቋማት፣አለም አቀፍ ድርጅቶች፣የግል ሴክተሮችና ማህበራት/ እንዲሁም
- እህት ከተሞች ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

## 7. የሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን ዋና ዋና ተግባራት

### 7.1 የከተሞች ኤግዚቢሽን እና ከተማን የማስተዋወቅ (City Marketing) ዉድድር

**ዓላማ፡** ከተሞች የልማት ስራዎቻቸውን ይዘው የሚቀርቡበት፣ እርስ በእርስ የሚማማሩበት ብሎም የኢንቨስትመንትና የቱሪዝም መስህቦቻቸውን የሚያስተዋውቁበት ነው፡፡

በሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን ኤግዚቢሽን ከተሞች ያስመዘገቧቸውን ዉጤቶችና መልካም ስራዎቻቸውን ይዘው ይቀርባሉ፡፡ በዚህ ኤግዝቢሽን ተሳታፊ የሚሆኑ ከተሞች ከዋና ዋና የልማት አጋሮቻቸውና ባለድርሻዎች እንዲሁም ከእህት ከተሞቻቸው ጋር የሚያከናውኗቸውን ስራዎች ይዘው ይቀርባሉ፡፡ ይህ ዝግጅት ከተሞች ራሳቸውን የሚያስተዋውቁበት፣ ስለውጤቶቻቸው ለከተማ ነዋሪዎች መረጃ የሚሰጡበት ብሎም እርስ በእርስ የሚማማሩበትና ልምድ የሚቀስሙበት ሲሆን ኤግዚቢሽኑ የሚመራበት ወጥ መመሪያ ተዘጋጅቶ የሚከናወን ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ከተሞች ራሳቸዉን በማስተዋወቅ በሚያደርጊት ጥረት ዉድድር ይካሄዳል፡፡

**አስተባባሪ፡** የበዓሉ ዝግጅት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ህዝብ ግንኙነት መምሪያ አስተባባሪነት፣ በሚ/ር መ/ቤቱ የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ የስራ ሂደትና በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም በጂቲዜድ የቴክኒክ ድጋፍ ይከናወናል፡፡

## 7.2 የኢትዮጵያ ከተሞች የምርጥ ተሞክሮ ውድድር እና ሽልማት

ዓላማ፡ **በከተማ ልማት ፖሊሲና ፕሮግራሞች ትግበራ ዙሪያ የተመዘገቡ ውጤታማ ልምዶችን በመቀመር እና በማስፋፋት የከተማ ልማት ስኬትን ማፋጠን ብሎም በከተሞች መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስ መፍጠር፡፡**

ይህ ውድድር ከተሞች በልማት ፕሮግራሞቻቸው ትግበራ ዙሪያ ያስመዘገቧቸውን መልካም ተሞክሮዎች በማቅረብ የሚወዳደሩበትና የሚማማሩበት ነው፡፡ በውጤታማ ስራዎቻቸውም ላይ ጤናማ ፉክክር በማድረግም የሚማማሩበትና ለቀጣይ ስኬት የሚተጉበት ተግባር የሚከናወንበትም ይሆናል፡፡

አስተባባሪ፡ በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የፖሊሲና ፕሮግራም የስራ ሂደት ዋና አስተባባሪነት በሚ/ር መ/ቤቱ የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ የስራ ሂደት እና በጂቲዜድ ድጋፍ ይከናወናል፡፡

## 7.3 "ከተማዬ" የወጣቶች የፎቶግራፍ እና የስዕል ውድድር

ዓላማ፡ **ወጣቶች በከተማቸው ልማት ውስጥ ያላቸዉን ተሳታፊነት ማጎልበት ብሎም ስለከተሞቻቸው ያላቸውን የባለቤትነት ስሜት ማዳበር፡፡**

በሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን ከተለያዩ ከተሞች በተውጣጡ ወጣቶች መካከል የፎቶግራፍ እንዲሁም የስዕል ውድድር ይካሄዳል፡፡ ይህ ውድድር ወጣቶች ከተማቸውን የሚቃኙበትን እይታ የሚያመላክት ሲሆን ተሳትፏቸውን ለማበረታታትና ከተማቸውን በሚመለከት የእኔነት ስሜት እንዲያዳብሩ ለማድረግ ታቅዶ የተዘጋጀ ነው፡፡ የስዕል ተወዳዳሪዎች ሀሳቦቻቸውን ብቻ በመያዝ በበዓሉ ላይ በመገኘት በአከባበሩ ወቅት የሚቀርቡላቸውን የስዕል መሳሪያዎች በመጠቀም የሚያከናውኑት ውድድር ይሆናል፡፡

አስተባባሪ፡ በጂቲዜድ ዋና አስተባባሪነት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ህዝብ ግንኙነት መምሪያና በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ድጋፍ ይከናወናል፡፡

## 7.4 የሐዋሳ ከተማ የ50ኛ ዓመት ክብረ በዓል ማጠቃለያ

ዓላማ፡ **የሀዋሳ ከተማ የ50ኛ አመት መጠናቀቅን ምክንያት በማድረግ ከተሞች እና ነዋሪዎች ለአካባቢ ጥበቃ እና ልማት ይበልጥ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ**

በዚህ ዝግጅት የሀዋሳ ከተማ ጉብኝት ይካሄዳል፡፡ የሀዋሳ ከተማ ህዝብ ፓርክ የመሰረት ድንጋይ እና የመታሰቢያ የአረንጓዴ ልማት የችግኝ ተከላ ይከናወናል፡፡ የሀዋሳ ከተማን የሚመለከቱ ጥናታዊ ጽኁፎች ቀርበዉ ዉይይት ይካሄድባቸዋል፡፡ የእራት ዝግጅትና የሙዚቃ ኮንሰርት ይካሄዳል፡፡ መዝጊያ ንግግር እና የስንብት መልዕክት ይተላለፋል፡፡

አስተባባሪ፡ በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ዋና አስተባባሪነት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የሶሻል ኮሚቴ እና በጂቲዜድ ድጋፍ ይከናወናል፡፡

## 7.5 ሴሚናርና የፓናል ውይይት

ዓላማ፡ **በከተማ ልማት ፖሊሲና ፕሮግራሞች ትግበራ ዙሪያ ከተሞች ያጋጠሟቸዉን የጋራ ችግሮች የሚፈቱ የመፍትሔ አቅጣጫዎች መጠቆም፡፡**

የከተማ ልማት ፖሊሲ የትኩረት መስክ በሆኑት የከተማ ልማት ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ትግበራ ዙሪያ የሚያተኩሩ ሴሚናርና የፓናል ውይይቶች ይካሄዳሉ፡፡ የፖሊሲውና የፕሮግራሞች ውጤታማነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል በከተማ ልማት ዋና የልማት ተዋናዮች፣ በባለድርሻ አካላትና በከተማ ነዋሪው ዘንድ ግንዛቤ እንዲዳብር ይደረጋል፡፡ የፓናል ውይይቶቹ በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ይሆናሉ፡፡

- በከተሞችና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትብብር ማዕቀፍ ስር የምርጥ መመረቂያ ጽሁፎች ውድድር እና በውድድሩ አሸናፊ ጽሁፎች ላይ ዉይይት፣

- ባለፉት አምስት ዓመታት የተካሄዱ የከተሞች የአቅም ግንባታ ስራዎች ዳሰሳ/የተገኙ ዉጤቶች፡ ያልተቀረፉ ችግሮች እና የመፍትሄ አቅጣጫዎች/
- የሀዋሳ ከተማ የ50 አመት የእድገት ጉዞ
- የአዋሳ ሀይቅ ጥበቃ እና የልማት አማራጮች

አስተባባሪ፡ በኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ዋና አስተባባሪነት፣ በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ የስራ ሂደት እንዲሁም በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ድጋፍ የሚፈጸም ነው፡፡

## 7.6 የህዳር 17 የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን ሀገር አቀፍ በዓል ዝግጅት

ዓላማ፡ **የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በሁሉም ከተሞች ነዋሪዎች ዘንድ ታውቆና ታስቦ በልማት ስራዎች እንዲከበር ማድረግ፡፡**

የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በብሄራዊ ደረጃ በሀዋሳ ከተማ የሚከበር ሆኖ በተጨማሪም ሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች ነዋሪዎቻቸውን ባሳተፈ መልኩ በተመረጡ የልማት ክንውኖች ላይ በማተኮር የሚያከብሩት ይሆናል፡፡ ይህ ዝግጅት ህዳር 17 ቀን የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን ሆኖ እንዲከበር የተወሰነበትን ምክንያት፣ የበዓሉን ጠቀሜታ፣ ከበዓሉ የተገኙና የሚጠበቁ ውጤቶችን በሚመለከት በሀገር አቀፍ የሚዲያ አውታሮች ለህዝብ ማብራሪያና ገለፃ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

አስተባባሪ፡ በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙት መምሪያ አስተባባሪነት፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የፖሊስና ፕሮግራም የስራ ሂደት ድጋፍ የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 7.7 የመዝናኛ ዝግጅቶች

ዓላማ፡ **የተለያዩ የመዝናኛና የባህል ዝግጅቶችን በማቅረብ ለ2ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን ድምቀት መስጠት፡፡**

በሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን የከተሞችን ባህል ልምድና ታሪክ ብሎም እሴቶቻቸውን ያማከለ የመዝናኛና የሙዚቃ ዝግጅቶች የሚቀርቡበትና በዓሉ ሳይሰለች የሚከበርበት ይሆናል ፡፡

አስተባባሪ፡ በሀዋሳ ከተማ አስተዳደርና በጂቲዜድ የቴክኒክ ድጋፍ ይከናወናል፡፡

## 7.8 የኮሙኒኬሽንና የሚዲያ ፕሮግራም

ዓላማ፡ **የኢትዮጵያ ከተሞች ቀንን በማስተዋወቅ ግንዛቤ መፍጠርና ዝግጅቱ ሀገር አቀፍ ብሎም ዓለም አቀፍ እውቅና እና ሽፋን እንዲኖረው ማድረግ፡፡**

ይህ ዝግጅት ከተሞች በልማት ፖሊሲያቸው፣ ዕቅዶቻቸውና በፕሮግራሞቻቸው ዙሪያና እየተገበሯቸው ባሉት እንቅስቃሴዎች የተገኙ ውጤቶች እንዲታወቁ የሚያስችል ነዉ፡፡ በዝግጅቱ ከተሞች በልማት ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር ተባባሪነት ማጠናከር የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የኮሚኒኬሽን ስራዎች ይከናወናሉ ፡፡በዚህም ብዛት ያላቸዉ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የሚዲያ ተቋማት እንዲጋበዙና ሽፋን እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡፡ በአሉን በሚመለከት መግለጫ በሬድዮና በቴሌቭዥን መግለጫ ይሰጣል እንዲሁም መጽኄጽት ይዘጋጃል፡፡

አስተባባሪ፡ በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነት መምሪያ ዋና አስተባባሪነት፣ በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር፣ በጂቲዜድ የህዝብ ግንኙነት፣ በመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች እና በሚዲያ ተቋማት ድጋፍ ይፈጸማል፡፡

## 7.9 በከተሞች ኤችአይቪ/ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር

**ዓላማ:** **በከተሞች የኤችአይቪ/ኤድስ ስርጭትና ላይ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ በመስጠት የመከላከልና የመቆጣጠር እንቅስቃሴዎችን ማጠናከር።**

በዚህ ፕሮግራም ስለ ኤችአይቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር መረጃዎች ይሰራጫሉ፣ በበጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ  የኤችአይቪ ምርመራና የምክር አገልግሎት ይሰጣል።

**ፈጻሚ:** በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ግብረኃይል ዋና አስተባባሪነት፣ በጂቲዜድ እና በሀዋሳ ከተማ አሰተዳደር ድጋፍ ይከናወናል።

## 7.10 በከተሞች ልማት ዙሪያ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት

**ዓላማ:** **ሴቶች በከተሞች ልማት ሂደት ዉስጥ ያላቸዉን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማጠናከር፣**

ሴቶች በከተማ ልማት ፖሊሲና ፕሮግራም ትግበራ ዙሪያ ባደረጉት ተሳትፎና በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ያስመዘገቧቸውን ውጤቶች ይዘው የሚቀርቡበት እና ያበረከቱትን አስተዋጾ የሚያሳውቁበት ዝግጅት ነው።

**ፈጻሚ:** በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ሴቶች ጉዳይ መምሪያ ዋና አስተባባሪነት በጂቲዜድ ድጋፍ ይከናወናል።

## 7.11 የከተሞች ዳይሬክተሪ ዝግጅትና ምርቃት

**ዓላማ:** የከተሞችን አጠቃላይ ሁኔታ ለህበረተሰቡና ለልማት አጋሮች በማስተዋወቅ እና ግንዛቤ በመፍጠር ልማታቸውን ማፋጠን፣

ከተሞችን የሚገልጽና የሚያስተዋውቅ ስለከተሞች አጠቃላይ ሁኔታ ግልጽና የተሟላ ግንዛቤና እይታ የሚሰጡ መረጃዎች የሚቀርቡበት ይሆናል።

**ፈጻሚ:** በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነት መምሪያ ዋና አስተባባሪነት፣ በኮርፖሬት ሚዲያ ኮሚኒኬሽን እና በሀዋሳ ከተማ አስተዳደርና ድጋፍ ይከናወናል።

## 7.12 የሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን የመዝጊያ ፕሮግራም

**ዓላማ:** **የሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ዋና ዋና ክንውኖችንና የተገኙ ዉጤቶችን በመዳሰስ የበዓሉን ጠቀሜታ ይበልጥ የሚያጠናክር መልዕክት ማስተላለፍ።**

በ2ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን የመዝጊያ ፕሮግራም በበአሉ የተሳተፎ መድረኮች ለተሳተፉ፣ የላቀ ደረጃ ላስመዘገቡ እንዲሁም ለበአሉ ስኬታማነት የበኩላቸውን አስተዋጾ ላበረከቱ ባለድርሻዎች እንዲሁም ለውድድሮች አሸናፊዎች ሽልማቶችና ዕውቅና የሚሰጥበት ይሆናል። የ3ኛውን የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን አዘጋጅ ከተማም በዚህ የመዝጊያ ዝግጅት ወቅት ይመረጣል።

**ፈጻሚ:** የቴክኒክ ኮሚቴ

## 8. የ2ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በዓል የድርጊት መርሀ ግብር

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | ሰኔ/ሐምሌ | የክንውን ጊዜ ነሐሴ/ ጳጉሜ | | | | | መስከረም | | | | ጥቅምት | | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሳ1 | ሳ2 | ሳ3 | ሳ4 | ሳ5 | ሳ6 | ሳ7 | ሳ8 | ሳ9 | ሳ10 | ሳ11 | |
| 1 | ሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በአል አከባበር የጋራ የዕቅድ አዘጋጅ ኮሚቴዎች ማዋቀር | | | | | | | | | | | | | የሥራና ከተማ ልማት ሚነሰቴር ህዝብ ግንኙነት የሥራ ሂደትና የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ |
| 2 | የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በአል የሚከበርበትን መነሻ ዕቅድ ማዘጋጀት | | | | | | | | | | | | | የስ.ከ.ል.ሚ/ር ህዝብ ግንኙነት የሥራ ሂደት፣ የኢት.ከ.ት.መ የሀዋሳ ከተማ |
| 3 | ለሁለተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በዓል የተዘጋጀውን የጋራ ዕቅድ በስራና ከተማ ልማት ሚነስቴር አቅርቦ ማስጸደቅ | | | | | | | | | | | | | የስ.ከ.ል.ሚ/ር ህዝብ ግንኙነት የሥራ ሂደት፣ የኢት.ከ.ት.መ እና የሀዋሳ ከተማ |
| 4 | የበአሉ አፈጻጸም ፣ዝርዝር ዕቅድ ማውጣትና ማጸደቅ | | | | | | | | | | | | | ቴክኒክ ኮሚቴ |
| 5 | ለከተሞች ቀን በአል ዝግጅት የሚያስፈልጉ የተለያዩ የአፈጻጸም መመሪያዎችን ማዘጋጀት | | | | | | | | | | | | | ቴክኒክ ኮሚቴ |
| 6 | ለከተሞች ቀን በአል ዝግጅት የተዘጋጁ መመሪያዎችን ማስጸደቅ | | | | | | | | | | | | | አብይ ኮሚቴ |
| 7 | በኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በአል የሚሳተፉ ከተሞችንና ባለድርሻ አካላትን መለየት | | | | | | | | | | | | | ቴክኒክ ኮሚቴ |
| 8 | በኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በአል ለሚሳተፉ ከተሞችና ባለድርሻ አካላት ጥሪ ማስተላለፍ | | | | | | | | | | | | | ቴክኒክ ኮሚቴ |
| 9 | በከተሞች ቀን በአል የሚሳተፉ ከተሞችንና ባለድርሻ አካላትን ማሳወቅ፣መደገፍ እና ክትትል ማድረግ፣ | | | | | | | | | | | | | ቴክኒክ ኮሚቴ |
| 10 | ህዳር 17 ቀን 2003 ዓም ሀገር አቀፍ በአል ሆኖ እንዲከበር ለከተሞች ጥሪ ማስተላለፍ | | | | | | | | | | | | | አብይ ኮሚቴ |
| 11 | በኢትዮጵያ ከተሞች ቀን ምርጥ ተሞክሮዎችንና ስኬታማ ስራዎችን ይዘው ለሚቀርቡ ከተሞች ድጋፍና እገዛ ማድረግ | | | | | | | | | | | | | የቴክኒክ ኮሚቴ |
| 12 | በኢትዮጵያ ከተሞች ቀን የሚቀርቡ የኢግዝቢሽን ዝግጅት ለሚሳተፉ ከተሞች | | | | | | | | | | | | | ቴክኒክ ኮሚቴ |

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | ሰኔ/ሐምሌ | የክንውን ጊዜ ነሐሴ/ ጳጉሜ | | | | | መስከረም | | | | ጥቅምት | | አከናዋኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሳ1 | ሳ2 | ሳ3 | ሳ4 | ሳ5 | ሳ6 | ሳ7 | ሳ8 | ሳ9 | ሳ10 | ሳ11 | |
| | ድጋፍና እገዛ ማድረግ | | | | | | | | | | | | | |
| 13 | በኢትዮጵያ ከተሞች ቀን ለመወዳደር የሚቀርቡ ወጣቶች የስዕልና የፎቶግራፍ ድጋፍና እገዛ ማድረግ | | | | | | | | | | | | | የቴክኒክ ኮሚቴ |
| 14 | በኢትዮጵያ ከተሞች ቀን ለውይይት የሚቀርቡ ርዕሰ ጉዳዮችን፣አቅራቢዎችንና ተሳታፊዎችን መለየትና ፕሮግራሙን ማካሄድ | | | | | | | | | | | | | አብይ ቴክኒክና አብይ ኮሚቴ |
| 15 | የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በአልን አስመልክቶ የኮሚኒኬሽን ስራዎችን ማስፈጸም | | | | | | | | | | | | | የቴክኒክ ኮሚቴ |
| 16 | የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በአል የሚካሄድበትን ቦታ መምረጥ፣ምቹነቱን በጉብኝት ማረጋገጥና አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማመቻቸት | | | | | | | | | | | | | የሀዋሳ ከተማና የቴክኒክ ኮሚቴ |
| 17 | ለኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በአል አስፈላጊ የሎጅስቲክ እና የቴክኒክ ድጋፍ መለየት፣ማመቻቸት፣ማሰተባበር፣ ድጋፍና ክትትል ማድረግ | | | | | | | | | | | | | የቴክኒክ ኮሚቴ |
| 18 | ለኢትዮጵያ ከተሞች ቀን በአል ዝግጅት መልዕክቶችን መለየት፣ማዘጋጀት፣እንዲተላለፍ ማድረግ | | | | | | | | | | | | | አብይ ቴክኒክና ኮሚቴ |
| 19 | የቴክኒክ ኪሚቴ የስራ አፈጻጸም ሂደት ሪፖርት ለአብይ ኮሚቴ ያቀርባል። | | | | | | | | | | | | | አብይ የቴክኒክና፣ ኮሚቴ |